# ከክብረ-ማርያም ለተላከው እ-ጦማር የተሰጠ መልስ፡-

የቤተሰብዎን ደኅንነት ያሳወቀን እ-ጦማርዎ ስለደረሰን፡ እጅግ ደስ አለን፤ እግዜር ይስጥልን! ኹላችንንም በያለንበት የሚጠብቀን፡ ቸሩ ፈጣሪያችን፡ ከቅድስት እናቱ ጋር ይክበር ይመስገን፡ እኛም እንደእናንተ፡ በመልካም ኹኔታ ላይ እንገኛለን።

በጥንታዊዋና በእውነተኛዋ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊት ተዋሕዶ ሃይማኖታችን ጸንተን የምንኖረው፡ እኛ ኪዳናውያን ኢትዮጵያውያንና ኪዳናውያት ኢትዮጵያውያት፡ የድንግል ማርያምንና የኢየሱስ ክርስቶስን የልደት በዓል የምናከብረው እኮ፡ በመስከረም ፩ (አንድ) ቀን ነው። የትስብእቱን፡ (ማለትም፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ በሊቀ መላእክት፡ ቅዱስ ገብርኤል የምሥራች ቃል፡ በእመቤታችን ማሕፀን የተፀነሰበትን) በዓል ደግሞ የምናከብረው፡ በታኅሣሥ ፩ (አንድ)፥ እመቤታችን የተፀነሰችበትንም፡ በታኅሣሥ ፯ (ሰባት) ቀን ነው። አኹን ያለንበት ወራት እኮ፡ እነዚህን በዓላት አክብረን፡ በጥር ፲፩ ቀን እስከምናከብረው እስከበዓለ ጥምቀቱ ድረስ፡ ከጾመ ማርያም ጋር፡ "ዮም ፍሥሓ ኮነ! በእንተ ትስብእቱ ለኢየሱስ ክርስቶስ! ተፈጸመ ትስብእት፡ በማርያም ድንግል! በብሥራተ ገብርኤል፡ ዜናዌ ቃል!" እየተባባልን፡ መንፈሳዊ ደስታችንን የምንገልጽበት ነው።

የጌታችንን ልደት፡ በታኅሣሥ ፳፰ እና/ወይም ፳፱ ቀን፥ የእመቤታችንንም ልደት፡ በግንቦት ፩ ቀን "ይከበር!" ብለው፡ ከትክክለኛው መስከረም ፩ ቀን፡ አላገባብ፡ በማናለብኝ ድፍረት ያዛወሩት፡ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ላይ የገዢነት ሥልጣንና ኃይል የተሰጣቸው፥ በእስልምና ገዢዎቻቸውና በፈረንጆች ድጋፍ የሚመሩት፡ የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ጳጳሳት ናቸው። ይህን፡ የታኅሣሡን ቀን የመረጡትም፡ ቀድሞ፡ በአረማዊነት አምልኳቸው ጊዜ፡ የጣዖታቸውን በዓል የሚያከብሩበት ወርና ቀን ስለኾነ ነበር።

የዚህ ኹሉ ዝርዝር ሓተታና ሙሉ ትንተና፡ በመጻሕፍቴ፥ በተለይም፡ "ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፍረጃ!" እንዲሁም፡ "ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት" በሚለው፡ "በኹለተኛው መጽሓፍ"፡ በሚበቃ ተገልጾና ተብራርቶ ይገኛል። ስለዚህ፡ እነዚህን ጽሑፎች፡ እስካኹን አልተመለከትሻቸው ከኾነ፡ ነገሩ፡ ሃይማኖታችንን የሚመለከት ነውና፡ በማስተዋል ልታነብቢያቸው ያስፈልጋል።

ጾመ ማርያምን፡ በሰላም አስፈጽሞና ለበዓለ አስተርእዮው፡ በደኅና አድርሶ፡ በብርሃነ ጥምቀቱ ደስታ፡ ታላቁ በዓላችንን፡ በያለንበት፡ በሓሤት ለማክበር ያብቃን!

ንቡረ-እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ፤
በቅዱሱ ኪዳን፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ አገልጋይ።

---